በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፡

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሣብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሣብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች የሥራ አመራር ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የገቢ ሂሳብ

1.1 በገቢ የሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ

1.1.1 ግኝት

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6(ሐ) እና አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8(ሠ) በፋይናንስ ምንጮች የተመዘገቡ ሂሳቦች ሚዛን ተወስዶ ወርሀዊ ዓመታዊ ሪፖርቶች ማዘጋጀት እና የተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር መቅረብ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርት ተካቶ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ከውጭ ሀገር የሚመጡ ተመራማሪዎች ለምርምር ከሚከፈላቸው ሂሳብ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ገቢ ያደረጉት ሂሳብ ብር 6,718,714.45
- ለጥናትና ምርምር የማመልከቻ ፎርም ብር 148,816.31

በድምሩ ብር 6,867,530.76 ብሄራዊ ባንክ በሚገኘው የባንክ ቁጥር 0100181040093 ገቢ የተደረገ ቢሆንም እስከ ጥር 25, 2009 ሂሳቡ የተሰበሰበው ባለሥልጣኑ ባሳተመው ደረሰኝ ሲሆን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኙ እንዲታተም ከሚመለከተው አካል የተፈቀደበት ደብዳቤ ያልቀረበ እንዲሁም በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ያልተመዘገበ እና ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሚያቀርበው የገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡

1.1.2 ስጋት

በባለሥልጣኑ የተሰበሰበው የገቢ ሂሳብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለታቀዱ ተግባራት ማስፈጸሚያ ለማካተት ካለመቻሉም በላይ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉንም ለመቆጣጠር አያስችልም፡፡ በተጨማሪ የቀረበው የሂሳብ ሪፖርት የበጀት ዓመቱን የስራና የፋይናንስ እንቅስቃሴ በትክክል ስለማያሳይ በሂሳብ ሪፖርት በመንተራስ ውሳኔ የሚሰጥ የመረጃ ተጠቃሚ የተሳሳተ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

1.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ለወደፊቱ ማንኛውም የመንግስት ገቢ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ተመዝግቦ ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተሰበሰበው ገቢ በሙሉ ወደ ባንክ ገቢ መደረጉ እና አለአግባብ ወጪ ያልተደረገ መሆኑ ተጣርቶ ፈሰስ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.1.4 የሥራ አመራር ምላሽ

የጥናትና ምርምር ሂሳብ የተከፈተው ከአስጠኚዎች የሚሰበሰበው ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ገቢ ለማድረግ ሳይሆን ጥናቱ የሚካሄድባቸው ክልሎች ያሉትን የቅርስ ቦታዎች ለማልማት መደቡ “A” የሆነ በዓመቱ መጨረሻ ብሎክ የማይደረግ (ፈሰስ) የማይሆን የባንክ ሂሳብ ተከፍቶ ገቢ የሚደረግ መሆኑን እና፣ ሂሳቡ የራሱ የሆነ መዝገብ ያለው ሪፖርቱም ለውስጥ ኦዲቱ እንደሚቀርብ የገለፁና በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ቢካተት እና ፈሰስ ቢደረግ ገንዘቡን ለጥናቱ ገቢ የሚያደርጉ አካላት ላይስማሙ ስለሚችሉ ገቢው ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል በመሆኑ ሊታሰብበት እንደሚገባ እና ፈሰስ ሊደረግ የሚገባ ከሆነ በኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

2. የወጪ ሂሳብ

2.1 የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈፀመ ግዥ

2.1.1 ግኝት

የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ ሰኔ 2/2002 ክፍል 4 አንቀፅ 24.3 የመንግስት መ/ቤቶች በዋጋ ማቅረቢያ ዘዴ ግዥ ሲፈጽሙ አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡ መካከል ቢያንስ ከሦስቱ የዋጋ ማቅረቢያ በመጠየቅ ዋጋቸው ተወዳድሮ አነስተኛ ዋጋ ያቀረበው ተመርጦ በበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚወክላቸው ሰዎች እንዲፀድቅ በማድረግ ግዥ ማከናወን እንደሚችሉ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ 9 የወጪ ቫውቸሮች ለመድረክ አስተዋዋቂ፣ ለመስተንግዶ እና ለአዳራሽ ኪራይ የዋጋ ማቅረቢያ/ፕሮፎርማ/ ሳይሰበሰብ እና ውድድር ሳይደረግ ብር 881,282.14 የሚያወጣ የአገልግሎት ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡(ዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

2.1.2 <u>ስጋት</u>

ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ግዥ መፈፀም ፍትሐዊ የገበያ ውድድር እንዳይኖር ሊያደርግ ከመቻሉም በላይ መንግስት ከሌሎች አቅራቢዎች ሊያገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል ፡፡

2.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ማንኛውም ግዥ በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2.1.4 <u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

በየክልሎቹ በቅርሶች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ሲሰጥ ቀደም ሲል በነበረው አሰራር ለስብሰባው አመቺ የሆነውን ሆቴልና አዳራሽ በመምረጥ ይካሄድ ነበር፡፡ ነገር ግን በኦዲተሮች ማስተካከያ እንዲደረግ አስተያየት ከተሰጠ ጀምሮ የዋጋ ማቅረቢያ በመሰብሰብና ቃለጉባዔ ተይዞ በማወዳደር የሚካሄድ መሆኑን በመውጫ ውይይቱ ወቅት ገልጸዋል፡፡

2.2. <u>ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

2.2.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 2 አገልግሎቱ በተፈለገው ስፔስፊኬሽን መሠረት መቅረቡ ወይም አገልግሎቱ መሰጠቱ ሲረጋገጥ እና እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ተ.ቁ 2/ለ መሰረት ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብ እና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ተጠቅሷል፡፡ ሆኖም በ2009 በጀት ዓመት በተለያዩ ክልሎች ዞንና ወረዳዎች ለሚገኙ ጥንታዊ ቅርሶች ጥገናና እድሳት ጥበቃና እንክብካቤ አገልግሎት በባንክ የተላለፈ በድምሩ ብር 22,855,986.00 በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ በኦዲት እንደተረጋገጠው፡-

- በጀቱ ከመላኩ በፊት ጥገናና እድሳት የሚደረግለት ቅርስ ስምና የሚገኝበት ቦታ፣ የሚከናወነው ስራ፣የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን፣ ስራውን በበላይነት የሚመራውና የሚቆጣጠረው የመንግስት አካል/መ/ቤት እና ስራውን የሚያሰሩት

ሰዎች ስም ወዘተ በዝርዝር የሚገልጽ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ገንዘቡ በሚላክለት አካል እየተዘጋጀ ለባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች የማይቀርብ መሆኑ፡-

- ገንዘቡን የላከው የመንግስት መ/ቤት እና ገንዘቡ የተላከለት አካል ኃላፊነትና ግዴታ የሚገልጽ የመግባቢያ ሰነድ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፡
- በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ኤጀንሲ የተላከው ገንዘብ ለተላከለት አካል ለመድረሱ በአብዛኛው የገቢ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፤ እንዲሁም ለቅርስ እድሳት/ጥገና/ጥበቃ እና እንክብካቤ ወዘተ… አገልግሎት ወጪ የተደረገውን ሂሳብ የሚገልጹ የሂሳብ ሰነዶች ደጋፊ የክፍያ ማስረጃዎች የገቢና የወጪ ሂሳብ ሪፖርቶች ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለኦዲት ስራ ሊያቀርብ አለመቻሉ፤
- በተለያዩ ክልሎች ዞንና ወረዳዎች ለሚገኙ ጥንታዊ ቅርሶች ጥገናና እድሳት ጥበቃና እንክብካቤ የተላከው ገንዘብ ለታቀደው ዓላማ ለመዋሉ በባለስልጣኑ የውስጥ ኦዲት እንደሚረጋገጥ ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም የጎንደር ባህል ቱሪዝም የ2006 እና የ2007 ሂሳብ እና የአክሱም ከተማ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ከ2006-2008 በጀት ዓመት የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በስተቀር ለኦዲት ያልቀረበ በመሆኑ ለጥንታዊ ቅርሶች ጥገናና እድሳት ጥበቃና እንክብካቤ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተላከው ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል አጥጋቢ አሰራር ባለመኖሩና ሂሳቡም በዝርዝር ኦዲት ባለመደረጉ በጉዳዩ ላይ አስተየያታችንን መስጠት አልቻልንም፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ 2 ይመልከቱ)

2.2.2 <u>ስጋት</u>

ማንኛውም ሂሳብ የተሟላ ደጋፊ የክፍያ ማስረጃ መኖሩ ሳይረጋገጥ መመዝገብ የገንዘብ ጥፋትና ጉድለት እንዲፈጸም ሊገፋፉ ይችላል፡፡

2.2.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሊመዘገብ እና ማስረጃ ሲቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡ በወጪ ለተመዘገበው ሂሳብ ደጋፊ የክፍያ ማስረጃ እንዲቀርብ እና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይፈጸም ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.2.4 <u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

በ2008 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በፀደቁት ደንቦች መሰረት በላሊበላ፣ በአክሱም፣ በጉንደር እና በጢያ የዓለም አቀፍ ቅርሶች በባለስልጣኑ ስር የሚተዳደሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማቋቋም እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ ይህንንም ደንብ መሰረት ተደርጎ ጽ/ቤቶቹን በማቋቋም ጽ/ቤቶቹን የሚመሩ ሀላፊዎች እና ፈጻሚዎች ለመቅጠር ማስታወቂያ ወጥቶ ሰራተኞቹን አወዳድሮ ለመቅጠር በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን የእነዚህ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መከፈት ለቅርስ ጥበቃ እንክብካቤ ለጥገና የሚላኩ በጀቶችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማስተዳደር የሚያስችል ሲሆን አስፈላጊዎቹን የውክልና የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርቶች ሰነዶች በወቅቱና በጊዜው ማቅረብ እና ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆኑ ቅርሶቹን በቅርብ ሆኖ መጠበቅና መንከባከብ እንዲሁም ማስተዳደር ያስችላል፡፡ ቅርሶቹ እየሰጡ የሚገኙትን አገልግሎት እየቀጠሉ ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፍ ያደርጋል ተብሎ የሚታመን መሆኑን እና በተጨማሪም ሁሉም የገንዘብ ጥያቄ የሚቀርብባቸው መካነ ቅርሶች የጥገና ጥናት ሰነድ እና ፕሮፖዛል እንዲኖራቸው የሚያደርግ እና ማስረጃ ሳይቀርብባቸው በወጪ የሚመዘገቡ ሂሳቦች እንዳይኖሩ ያደርጋል በማለት በመውጫ ውይይት ወቅት ገልጸዋል፡፡

2.3 <u>ባልተፈቀደ መመሪያ ለጽሁፍ አቅራቢ እና ለአሰልጣኝ የተከፈለ</u>

2.3.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1994 ክፍል 6 ተራ ቁጥር 1-2 ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት ሰራተኞች ስልጠና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚሰለጥኑበትን ሁኔታ የሚመለከት ፖሊሲ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ባልፀደቀ የትምህርት እና ስልጠና መመሪያ በባህርዳር፣ በአዲግራት፣ በአሶሳ እና በላሊበላ ከተማ በተዘጋጀው ስልጠና የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሠራተኞች በአወያይነት እና በፅሁፍ አቅራቢነት ለተሣተፉበት በድምሩ ብር 75,000.00 የከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)

2.3.2 <u>ስጋት</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሳይጸድቅ እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሳይፈቀድ ክፍያ መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲባክን ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

2.3.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በስራ አመራሩ የተዘጋጀው የውስጥ መመሪያ በአፋጣኝ ለሚንስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ እንዲፈቀድ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም በሚመለከተው አካል ባልተፈቀደ መመሪያ ክፍያ እንዳይፈፀም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.3.4 <u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በየክልሉ ስልጠና ሲሰጥ በስልጠና ላይ የስልጠና ሞጁል ለሚያዘጋጁ፤ ስልጠና የሚሰጡና ለፅሁፍ አቅራቢዎች መ/ቤቱ ባወጣው የውስጥ መመሪያ የመ/ቤቱን የበላይ ኃላፊ በማፀደቅ ክፍያ ሲፈፀም እንደቆየ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በተሰጠው አስተያየት መሰረት ከ2010 በጀት አመት ጀምሮ እንዲቋረጥ ወይም እንዲቆም የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

2.4 <u>አላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል</u>

2.4.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት ሰኔ 2004 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀጽ 5 ተራ ቁጥር 3 መስሪያ ቤቱ የምግብ ወይም የመኝታ አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ የሰጠው አገልግሎት ሂሳብ በተፈቀደው ተመን መሰረት ከውሎ አበል ተቀናሽ መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሆኖም በአክሱም፣ በአሶሳ፣ በላሊበላ እና በደብር ብርሃን ከተማ በተካሄደው ስልጠና ተሳታፊዎቹ የምሳ መስተንግዶ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የቀረበላቸው ቢሆንም አለአግባብ የምሳ አበል ብር **34,479.50** የተከፈላቸው ሲሆን ባለፈው በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ 4 ይመልከቱ)

2.4.2 <u>ስጋት</u>

ከውሎ አበል መመሪያ ውጭ ክፍያ መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲባክን ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡እንዲሁም መንግሥት ያወጣውን መመሪያ ተከትሎ ክፍያ ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

2.4.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጸም መንግሥት ያወጣውን የውሎ አበል መመሪያ መሰረት ማድረግ ይገባል፡፡ አለአግባብ የተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ እና ተመሳሳይ ሁኔታ በድጋሚ እንዳይፈጸም ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.4.4 የሥራ አመራር ምላሽ

በየክልሉ ስልጠና ሲሰጥ የውሎ አበል ተከፍሎ የምሳ መስተንግዶ የተደረገው ሰልጣኞቹ ስልጠናውን በትኩረት እንዲከታተሉ፤ ምሳ ፍለጋ እንዳይጉላሉና የስልጠናው ዓላማ ግቡን እንዲመታ በማሰብ ሲሆን የኦዲት ሪፖርቱ ከደረሳቸው በኋላ እንዲቆም የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

3. ተሰብሳቢ ሂሳብ

3.1. ግኝት

በፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 4(ለ) መሰረት ለስራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁን እንጂ በሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው 4,032,078.99 ውስጥ በሂሳብ መደብ 4201 ብር 19,122.00 ከ1ዓመት ከ6 ወራት በላይ የቆየ ውዝፍ ያልተሰበሰበ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ 5 ይመልከቱ)

3.2 ስጋት

በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል፡፡

3.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ተሰብሳቢ ሂሳቡ እንዲሰበሰብ ተገቢው ጥረት እንዲደረግ እና ማስረጃው እንዲቀርብ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.4 <u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

የመ/ቤታችን ባልደረባ የነበረው ግለሰብ ለመንግስት ስራ ጉዳይ ወጪ አድርጎ ስራውን ሰርቶ ከተመለሰ በኋላ ሂሳቡን ሳያወራርድ በግሉ ወደ ውጪ ሃገር ሄዱ ሳይመለስ በዚያው የቀረ በመሆኑ ማስታወቂያ በተደጋጋሚ በማውጣት ሊቀርብ ስላልቻለ ለህግ ክፍል ተመርቶ በክትትል ላይ መሆኑን እና ለወደፊቱ ትኩረት እንዲሰጥበት ገልፀዋል፡፡

5. <u>የበጀት ሂሳብ</u>

5.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር አንድ ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሆኖም ለባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ከተደለደለው በጀት በዋና ዋና በጀት አርዕስቶች ከ10% በላይ

6200	የመደበኛ በጀት	11,407,298.15	
	የካፒታል በጀት	5,643,230.80	17,050,528.95
6300	የመደበኛ በጀት		1,712,668.70
		ድምር	18,763,197.65

በጠቅላላ ብር 18,763,197.65 ያልተሰራበት በጀት መገኘቱ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)

5.2 <u>ስጋት</u>

የተደለደለውን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ አለማዋል የባለስልጣኑን የበጀት ዓመቱን የስራ እንቅስቃሴ እና የፋይናንስ አስተዳደር ላይ እንዲሁም መንግስት ለሌሎች መሠረታዊ ለሆኑ ስራዎች በሚደለድለው በጀት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

5.3 <u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

በሥራ ላይ ሊውል የማይችል በጀት ማስፈቀዱ አግባብ ባለመሆኑ ለወደፊቱ በጥናትና በመረጃ የተደገፈ የበጀት ዕቅድ እንዲዘጋጅ ቢደረግ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ሊረዳ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የተፈቀደው በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል እንዲቻል በበጀት አጠቃቀምና አፈፃፀም ላይ ተገቢው ወቅታዊ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

5.4 የሥራ አመራር ምላሽ

ለመስክ ስራ የተሽከርካሪ እጥረት በመኖሩ የመስክ ቆይታ ጊዜ በማጠሩ የተያዘውን በጀት መጠቀም ካለመቻሉም በላይ የስራና የግዥ ጨረታ ወጥቶ ስራ ባለማለቁ ምክንያት፤ገበያ ላይ የቅርሶች ማስቀመጫ ሾው ኬዝ ባለመገኘቱና በብሄራዊ ሙዚየም ለሽያጭ የሚውሉ የስጦታ ዕቃዎች በግምጃ ቤት ስላሉ ተጨማሪ ህትመት ባለመካሄዱ እና አብዛኛው አላቂ ዕቃዎች በማዕቀፍ ግዥ በዋጋ ቅናሽ በመገኘታቸው ተራፊ በጀት ሊታይ መቻሉን ገልፀዋል፡፡

6. ንብረት አስተዳደር

6.1 አላቂና የቋሚ ንብረት

6.1.1 ግኝት

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 05 ንዑስ አንቀጽ 2 የአላቂ እና የቋሚ ንብረት ቆጠራ ተደርጎ ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር መመዛዘን እንዳለበት እንዲሁም በዚሁ መመሪያ ክፍል አራት አንቀጽ 09 ንዑስ አንቀጽ1 (ሀ-መ) አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተሰብስበው ስልጣን በተሰጠው የመንግስት አካል መወገድ እንደሚኖርባቸው ይገልጻል። ይሁን እንጂ የንብረት ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከተው ተገኝቷል፡፡

- የ2009 በጀት ዓመት የቋሚ እና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የተጠናቀቀ ቢሆንም የኦዲቱ ስራው እስከተጠናቀቀበት ድረስ የቆጠራው ውጤት የንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ከሚያሳየው ከወጪ ቀሪ ጋር ስላልተመሳከረ ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በንብረት ክፍል ውስጥ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ 22 ላፕቶፕ፣ 24 ዴስክቶፕ ኮምፒውተር ፣16 ፕሪንተሮች፣ 28 የሴኩሪት ካሜራ ፣53 ጎማዎች፣ 40 ዲጂታል ካሜራዎች እና ሌሎች ብዛት ያላቸው ልዩ ልዩ ንብረቶች በንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

6.1.2 ስጋት

በንብረት ሂሳብ ላይ ወቅታዊ ክትትልና ቁጥጥር ካልተደረገ የንብረት ጥፋትና ጉድለት ቢከሰት በወቅቱ ላይደረስበት ይችላል፡፡ እንዲሁም ንብረቶች ሳይጠገኑ ወይም ሳይወገዱ በቆዩ ቁጥር ለተጨማሪ ብልሽት እና ጥፋት ሊጋለጡ ይችላሉ ፡፡

6.1.3 የማሻሻያ ሃሣብ

የቆጠራ ውጤቱን ከንብረት መዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ፣ እንዲሁም ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ንብረቶች አስፈላጊው ጥገና ተደርጎላቸው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ሊጠገኑ የማይችሉ ንብረቶች በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሠረት እንዲወገዱ የስራ አመራሩ የእርምት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

6.1.4 የሥራ አመራር ምላሽ

- የ2009 በጀት ዓመት የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ተጠናቆ የቆጠራው ውጤት የንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ ከሚያሳየው ከወጪ ቀሪ ጋር እየተመሳከረ ትክክለኛነቱ እየተረጋገጠ ይገኛል፡፡
- በንብረት ክፍሉ ውስጥ አገልግሎት መስጠት ያልቻሉ 22 ላፕቶፖች፣ 24 ዴስክቶፖች፣ 16 ፕሪንተሮችና ፎቶ ኮፒ ማሽኖችን እንዲረከቡን ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ተክኖሎጂ ሚኒስቴር ደብዳቤ ጽፈንና በስልክም ጠይቀን ቦታ ስለሌለ እየጠበቅን ነው፡፡
- የ53 ጎማዎች ዝርዝር ለመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ልከን መልስ እየጠበቅን ነው፡፡
- 40 ዲጂታል ካሜራዎችና 28 የሴኩሪቲ ካሜራዎችን ከዚህ በፊት ለማስወገድ ጨረታ ወጥቶ ነጋዴዎች /ተጫራቾች/ የሰጡት ዋጋ ገማች ኮሚቴ ከሰጠው ዋጋ በታች በመሆኑ በድጋሚ ጨረታ አውጥተን ለማስወገድ በሂደት ላይ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

6.2 ተሸከርካሪ

6.2.1 ግኝት

በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) በተመለከተው መሰረት የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢው ጥገናና እንክብካቤ ሊደረግለት እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከሚገኙት ተሸከርካሪዎች ውስጥ የሰሌዳ ቁጥር 3-032 AID ፍሪላንድ ላንድሮቨር፣ የሰሌዳ ቁጥር 2-01993 እና ፔጆ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር የባለቤትነት ደብተር የሌላቸው፣ በንብረትነት ያልተመዘገቡ እና አገልግሎት የማይሰጡ በተጨማሪም ቶዮታ ላንድ ክሩዘር የሰሌዳ ቁጥር ያልተለጠፈበት መሆኑ ታውቋል፡፡

6.2.2 ስጋት

ንብረቶችን በባለቤትነት ተረክቦ በንብረትነት መዝግቦ በኃላፊነት የሚጠብቃቸው ከሌለ ሊጠፉ እና ጉዳት ሊደርስባቸው ከመቻሉም በተጨማሪ ሳይጠገኑ ወይም ሳይወገዱ በቆዩ ቁጥር ተጨማሪ ብልሽትና ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስባቸው ስለሚችል ከጥቅም ውጭ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

6.2.3 የማሻሻያ ሃሣብ

በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሠረት በወቅቱ እንዲወገዱ አልያም ንብረቶች ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ከሆነ የባለቤትነት ደብተር ችግር በአፋጣኝ የሚፈታበትና አስፈላጊው ጥገና ተደርጎላቸው ለአገልግሎት እንዲበቁ የሚቻልበት መንገድ እንዲፈለግ ስራ አመራሩ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

6.3.4 የሥራ አመራር ምላሽ

3-032 AID ፍሪላንድ ላንድሮቨር፤ 2-01993 ፔጆ የባለስልጣኑ መኪኖች አይደሉም ከክልል የመጡ እና አንድ ሀገር ጎብኚ ከባለስልጣኑ ቅጥር ወጪ ትቷት ከሀገር በመወጣቱ ወደ ቅጥር ግቢው ብናስገባውም ለማስወገድ ወይም ሰነድ ለማግኘት ባለመቻሉ ለረዥም ግዜ እርምጃ ሳይሰወሰድባቸው እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

6.3. የብሄራዊ ሙዚየም ጥበቃና እንክብካቤ በተመለከተ፡

6.3.1 ግኝት

በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) በተመለከተው መሰረት የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢው ጥገናና እንክብካቤ ሊደረግለት እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በቅድመ ታሪክ አሪክኦሎጂ እና ፒሊዬንቶሎጅ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ቅርሶች የውሃ እና የሽንት ቤት ፍሳሽ እየተንጠባጠበባቸው መሆኑ፤ ከሀንፃው እየተላጠ የሚወድቀው ፍርስራሽ የሚገኝ መሆኑ የኤክስሬይ ክፍል የነበረው በሽንት ቤቱ ፍሳሽ ምክንያት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፡ በተጨማሪም በዋናው የጎብኝዎች ሙዚየም የሚገኙት ቅርሶች የንጽህና ጉድለት የሚታይባቸውና በአቧራ የተሸፈኑ መሆናቸው በኦዲት ወቅት ታወቋል፡፡

6.3.2 <u>ስጋት</u>

ቅርሶች በንጽህና እና በእንክብካቤ ካልተያዙ ጉዳት ሊደርስባቸው ስለሚችል ታሪካዊነታቸውን ጠብቀው ለትውልድ እንዳይተላለፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

6.3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለቅርሶች አስፈላጊውን ጥበቃ እና ቁጥጥር በማድረግ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጣ ይገባል፡፡

6.3.4 <u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

ችግሩን በመረዳት የጥገና ስራ እንዲሰራ በጀት በማስፈቀድ በ2009 በጀት አመት መጨረሻ ጨረታ በማውጣት ዮት ኮንስትራክሽን ከተባለ ኮንትራክተር ጋር ውል በመዋዋል ከ2010 በጀት አመት ጀምሮ የዕድሳት ስራው የተጀመረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

7.1 <u>ከዩኒስኮ እና ከስፖንሰርሽፕ የተገኘ የፕሮጀክት ሂሳብ</u>

7.1.1 <u>ግኝት</u>

ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በመንግስት ከሚመደብለት በጀት በተጨማሪ ለተለያዩ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከዩኒስኮ እና ከስፖንሰር ሽፕ ብር 4,758,285.24 ገቢ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ሆኖም ሂሳቡ ለታለመለት አላማ ለመዋሉ በውጭ ኦዲተሮች የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት ሊቀርብ አልቻለም፡፡

ኦዲት አስደራጊዎች ተጠይቀው ሂሳቡን በሰጠው አካል እና በውስጥ ኦዲት ክፍል የሚታይ መሆኑን ቢገልፁም ይህን የሚያስረዳ ሰነድ ለኦዲት አልቀረበም፡፡

7.1.2 <u>ስጋት</u>

ሂሳቡ በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት የማይደረግ ከሆነ ገንዘቡ ለታቀደለት አላማ መዋሉን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

7.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከተለያዩ ድርጅቶች ያገኘው ገቢ ለታቀደለት አላማ ለመዋሉ ወይም የሚጠበቀውን ውጤት ለማስገኘቱ በውጭ ኦዲተሮች ሂሳቡን ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሪፖርቱን በተጠየቀ ጊዜ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

7.1.4 የሥራ አመራር ምላሽ

በመ/ቤታችን የስራ ክፍሎች ፕሮፖዛል ተሰርቶ ከዩኔስኮ የሚገኝ ፈንድ ሲገኝ እንደ ማንኛውም ገቢ ተመዝግቦ ወጪው ሲወጣ ሕጋዊ የግዥ መመሪያን ተከትለን ሥራ ላይ የምናውል ሲሆን፣ ሂሳቡም በውስጥ ኦዲተሮች ዕቅድ ከተያዘ እንደሚመረመርና ፕሮጀክቱን አግኝቶ ሥራ ላይ ያዋለው የሥራ ክፍል ፋይናንሽያል ሪፖርት በማዘጋጀት ወጪ የወጣባቸውን ዶክመንቶች እያንዳንዳቸውን ኮፒ በማድረግ ፈንዱን ለሰጣቸው አካል የሚላክ ሲሆን፣ የሪፖርቱ ቀሪ በየሥራ ክፍሎች የሚገኝ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

7.2 በ2008 በጀት ዓመት በኦዲት ውጤቶች ላይ የማስተካከያና የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው

7.2.1 ግኝት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰረት ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች፣ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸው እርምጃ ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው የተደነገገ ሲሆን በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 የመንግስት መ/ቤት ኃላፊ በውጭ ኦዲተሮችና እንዲሁም በውስጥ ኦዲት አገልግሎት በሚቀርቡት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ላይ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት በማድረግ በሰጠው የኦዲት ውጤትና የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት ተገቢው እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከታች የተመለከቱት እርምጃ ሳይወሰድባቸው ተገኝተዋል፡፡

- **አለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል**

  በባህር ዳር ከተማ፣ በአዳማ ከተማ እና በሃዋሳ ከተማ በተለያዩ ጊዜያት በተደረገው ስልጠና ላይ ለተገኙ ተሳታፊዎች ምሳ ቀርቦላቸው እያለ የሙሉ ቀን የውሎ አበል በድምሩ ብር 19,514.00 አላግባብ በመከፈሉ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ገንዘቡ ተመላሽ አልተደረገም፡፡

- **የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት**

  በተለያየ ክልል ለሚገኙ ቅርሶች ጥገናና እድሳት ፤ ለቀን ሰራተኞች ምንዳ እና እርዳታ ቀጥሎ በተዘረዘሩት የሂሳብ መደቦች በባንክ በኩል የተላከው ሂሳብ ብር 12,660,000.00 ደጋፊ የክፍያ ሰነዶችና አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ደጋፊ የሂሳብ ሰነዶችና ማስረጃዎች በባለስልጣኑ ስለማይጠበቁና ማስረጃዎቹን ሊያቀርብ ባለመቻሉ ሂሳቡን በዝርዝር ኦዲት ለማድረግም ሆነ ለክልሎች የተላከው ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን እንዲረጋገጥ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በጉዳዩ ላይ እርምት አልተደረገም፡፡

7.2 <u>ስጋት</u>

በኦዲት በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አለማድረግ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ እንዳይተገበር ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በላይ የመንግስት ገንዘብ እንዲባክን ሊያደርግ ይችላል፡፡

7.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት በወቅቱ ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ በስራ አመራሩ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

7.4 <u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

በተለይ በየክልሉ ለተሰጡ ስልጠናዎች የስልጠና ተከፋይ ከመላው አገሪቱ ወረዳዎች የሚመጡ በመሆኑ አግኝተን ለማስመለስ ከፍተኛ ችግር ስለሆነበቸው መሆኑን ገልጸው ለወደፊቱ በተሰጣቸው አስተያየት መሰረት ተገቢውን ጥንቃቄ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ስለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1 የዋጋ ማወዳደሪያ ያልቀረበለት

ተራ ቁ.	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የወጪው ምክንያት	ገንዘቡ የተከፈለው ድርጅት (ሰው) ስም	የንዘቡ ልክ
1	14/04/09	571170	6251	11 ጉባኤ ላይ ለኢንታንጀብል ቅርሶች የመድረክ አስተዋዋቂ	ለአቶ ግሩም ጫላ	40,000.00
2	24/04/09	885581	6271	በአክሱም ከተማ ለተዘጋጀው ስልጠና ከታህሳስ11-13/2009 ለምሳ፡ ለአዳራሽ ኪራይና ለሻይ ቡና	ለቦረና ሆቴል	65,279.51
3	07/06/09	885654	6271	በላሊበላ ከተማ ለተዘጋጀው ስልጠና ከጥር26-28/2009 ለምሳ፡ ለአዳራሽ ኪራይና ለሻይ ቡና	ለላል ቢዝነስ ሀውስ	74,698.41
4	13/07/09	885732	6271	በአሶሳ ከተማ ለተዘጋጀው ስልጠና ከመጋቢት 5-8/09 ለምሳ፡ ለአዳራሽ ኪራይና ለሻይ ቡና	ለብሌንዳና ሆቴል	112,400.38
5	15/09/09	885844	6271	በባህር ዳር ከተማ ለተዘጋጀው ስልጠና ከግንቦት 1-3/2009 ለአዳራሽ ኪራይና ለሻይ ቡና	ለዲናሎ ሆቴል	89,669.99
6	28/09/09	885870	6271	በላሊበላ ከተማ ለስልጠና ከግንቦት1-4/2009 ለሻይ ቡና መስተንግዶ	ለእየሩሳሌም እና ካፌ ሬስቶራንት	78,023.82
7	06/10/09	885884	6271	በደብረብርሀን ከተማ ከግንቦት 29-ሰኔ02/09 ለአዳራሽ ኪራይና ለሻይ ቡና	ለ ኢትዮ ባርኖስ ሆቴል	150,000.00
8	22/10/09	885926	6271	በአዲግራት ከተማ ለተዘጋጀው ስልጠና ከሰኔ 13-16/09 ለአዳራሽ ኪራይና ለሻይ ቡና	ለአሜና ገ/ስላሴ ሆቴል	101,023.95
9	13/07/09	885736	6271	በደብረበርሃን ከተማ ለተዘጋጀው ስልጠና መስተንግዶ	ዮሴፍ ሀይሉ ባለኮከብ ሆቴል	170,186.08
				ድምር		**881,282.14**

አባሪ 2 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት

ተራ ቁ.	ቀን	የወጪ ማስመስ ከሪያ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የወጪው ምክንያት	ገንዘቡ የተከፈለው ድርጅት (ሰው) ስም	የንዘቡ ልክ
1	17/04/2009	571186	6412	በአዲስ አበባ ስር ለሚገኝ የጻን አለም አጸደ ህጻናት ጥገናና እንክብካቤ ስራ	ለህጻን አለም መዋእለ ህጻናት ት/ቤት	360,000.00
2	05/10/2009	571517	6412	በደቡብ ወሎ ዞን ለሚገኝ ስላሴ ጥንታዊ ቤተክርስቴያን የጥገናና እንክብካቤ ስራ	ለመካነ ስላሴ ቤተክርስቴያን	250,000.00
3	05/10/2009	571518	6412	በትግራይ ክልል ለሚገኝ የጭሀ ስላሴ ቤተክርስቲያን የጥገናና እንክብካቤ ስራ	ለጭሀ ገዳም መካነ ህይወት ኪዳነምህረት	290,000.00
4	08/10/2009	571528	6412	በሰሜን ሸዋ ዞን በአንኮበር ወረዳ የሚገኘው የመድሀኒያለም ቤተክርስቲያን የጥገናና እንክብካቤ ስራ	ለሰሜን ሸዋ ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር	100,000.00
				ድምር		**1,000,000.00**
1	07/04/2009	571156	6244	በምእራብ ዞን ጎጃም ጎንጅ ቆለላ ወረዳ ለምትገኝ ወይዛዝርት ኪዳነምህረት ጥገናና እንክብካቤ	ለደብረ እንቁ ወይዛዝርት ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን	400,000.00
2	07/04/2009	571160	6244	ለኮንሶባህላዊ መልካ ምድር፡ለሀረር ቅርስ ቱሩዝም ቢሮ፡ላሊበላ፡ለአማራ ሴቶች ጉዳይ ቢሮ፡ለሰቆጣ አስተዳደርእና ለኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም	ለተለያዩ ክልሎች ቅርስ ጥገና	7,400,000.00
3	05/10/2009	571515	6244	በሰሜን ወሎ ዞን በመቄት ወረዳ ለምትገኝ ናዙኝ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ጥገናና እንክብካቤ	ለደብረገነት ናዙኝ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን	200,000.00
4	05/10/2009	571516	6244	በምእራብ ጎጃም ዞን በጎንጂ ለምትገኝ ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን የስእል ጥገና ስራ	ለደብረ እንቁ ኪዳነምህረት ህንጻ እድሳት	400,000.00
5	08/10/2009	571526	6244	በትግራይ ክልል፡በድሬደዋ	ለተለያዩ ክልሎች	4,320,000.00

				ከተማ አስተዳደር፡በፋሲል መዋኛ፡በላሰታ ወረዳና በሶዶጢያ ትክል ድንጋይ ቅርሶች ለመጠገን	ቅርስ ጥገና	
6	20/07/2009	571361	6244	በኢሊባቡር ዞን ጎሬ ከተማ ለሚገኘው የእንግሊዝ ቆንስላ ጽ/ቤት ለመጠገን	ለጎሬ ከተማ ለሚገኘው የእንግሊዝ ቆንስላ ጽ/ቤት	500,000.00
7	20/07/2009	571362	6244	በደቡብ ክልል ጎሙጎፋ ዞን ለምትገኘው ቋራ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ጥበቃና እንክብካቤ	ለቋራ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ህንጻ አሰሪ	230,000.00
8	21/07/2009	571367	6244	ለትግራይ ክልል ባህልና ቱሪዝምእና ለሰሜን ጎንደር ጎንደር፡	ለተለያዩ ክልሎች ቅርስ ጥገና	3,550,000.00
				ድምር		**17,000,000.00**
1	07/04/2009	571156	6114	በምእራብ ዞን ጎጃም ጎንጅ ቆለላ ወረዳ ለምትገኝ ወይዛዝርት ኪዳነምህረት ጥገናና እንክብካቤ	ለደብረ እንቁ ወይዛዝርት ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን	40,000.00
2	07/04/2009	571160	6114	ለኮንሶባህላዊ መልካ ምድር፡ለሀረር ቅርስ ቱሩዝም ቢሮ፡ላሊበላ፡ለአማራ ሴቶች ጉዳይ ቢሮ፡ለሰቆጣ አስተዳደርእና ለኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም	ለተለያዩ ክልሎች ቅርስ ጥገና	660,000.00
3	05/10/2009	571516	6114	በምእራብ ጎጃም ዞን በጎንጂ ለምትገኝ ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን የስእል ጥገና ስራ	ለደብረ እንቁ ኪዳነምህረት ህንጻ እድሳት	100,000.00
4	08/10/2009	571526	6114	በትግራይ ክልል፡በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር፡በፋሲል መዋኛ፡በላሰታ ወረዳና በሶዶጢያ ትክል ድንጋይ ቅርሶች ለመጠገን	ለተለያዩ ክልሎች ቅርስ ጥገና	700,000.00
5	20/07/2009	571361	6114	በኢሊባቡር ዞን ጎሬ ከተማ ለሚገኘው የእንግሊዝ ቆንስላ ጽ/ቤት ለመጠገን	ለጎሬ ከተማ ለሚገኘው የእንግሊዝ ቆንስላ ጽ/ቤት	100,000.00
6	20/07/2009	571362	6114	በደቡብ ክልል ጎሙጎፋ ዞን ለምትገኘው ቋራ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ጥበቃና እንክብካቤ	ለቋራ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ህንጻ አሰሪ	50,000.00
7	21/07/2009	571367	6114	በትግራይ ክልል ባህልና ቱሪዝምእና ለሰሜን ጎንደር ጎንደር፡	ለተለያዩ ክልሎች ቅርስ ጥገና	350,000.00

				ድምር		**2,000,000.00**
1	09/09/2009	571469	6271	በአማራ ብሄራዊ ክልል በባህል ቅርስ የምክክር ስልጠና	ለአማራ ብሄራዊ ክልል	130,800.00
2	04/05/2009	571210	6233	ለ11ኛ የዩኒስኮ የመክፈቻና መዝጊያ ፕሮግራም ለአማራና ለደቡብ ከክልል ሊመጡ ስለማይችሉ ለ128 ተሳታፊዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 5,000.00 እና ቦታው ድረስ በመሄድ ክፍያ ለፈጸሙት ለአበል የተከፈለ	ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴያትር	2,725,186.00
				ድምር		**2,855,986.00**
				ጠቅላላ ድምር		**22,855,986.00**

አባሪ 3 <u>ባልተፈቀደ መመሪያ የተከፈለ ለጽሁፍ አቅራቢ እና ለአሰልጣኝ</u>

ተቁ.	ቀን	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የወጪው ምክንያት	ለጽሁፍ አቅራቢ	ለአሰልጣኝ/አወያይ	ጠቅላላ ድምር
1	ኤፊሬም አማረ	15/9/09	JV885844	6271	በባህርዳር ከተማ ከግንቦት 01-03/2009 ለተዘጋጀ ስልጠና	2,000.00	500.00	2,500.00
2	ጥላሁን ገ/ስላሴ	15/9/09	JV885844	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
3	አበራ አንጀሎ	15/9/09	JV885844	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
4	ሠለሞን መለሠ	15/9/09	JV885844	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
5	ጌትዬ ተፈራ	15/9/09	JV885844	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
6	እስራኤል አራጌ	15/9/09	JV885844	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
7	የሺዋስ ደሳለኝ	15/9/09	JV885844	6271	›› ››	2,000.00		2,000.00
					ድምር	**14,000.00**	**3,000.00**	**17,000.00**
1	ጥላሁን ገ/ስላሴ	22/10/09	JV885926	6271	በአዲግራት ከተማ ከሰኔ 13-16/2009 ለተዘጋጀ ስልጠና	2,000.00	1,000.00	3,000.00
2	አበራ አንጀሎ	22/10/09	JV885926	6271	›› ››	2,000.00	1,000.00	3,000.00
3	ሠለሞን መለሠ	22/10/09	JV885926	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
4	ሰብለወንጌል ተክሉ	22/10/09	JV885926	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
5	ተመስገን ለታ	22/10/09	JV885926	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
6	ዝናሽከ ከፈያለው	22/10/09	JV885926	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
7	መላከጸሀይ ተስፋዬ	22/10/09	JV885926	6271	›› ››	2,000.00		2,000.00
					ድምር	**14,000.00**	**4,000.00**	**18,000.00**
1	ኤፍሬም አማረ	24/4/09	JV885581	6271	በአክሱም ከተማ ከታህሳስ 11-13/2009 ለተዘጋጀ ስልጠና		1,000.00	1,000.00
2	ጥላሁን ገ/ስላሴ	24/4/2009	JV885581	6271	›› ››		1,000.00	1,000.00
3	አበራ አንጀሎ	24/4/2009	JV885581	6271	›› ››		1,000.00	1,000.00
4	ጌትዬ ተፈራ	24/4/2009	JV885581	6271	›› ››		1,000.00	1,000.00
5	መስፍን ጌተ	24/4/2009	JV885581	6271	›› ››		1,000.00	1,000.00

6	ፍስሀጽዮን ተካ	24/4/2009	JV885581	6271	›› ››		1,000.00	1,000.00
7	ተክለወይን ተስፋዬ	24/4/2009	JV885581	6271	›› ››		1,000.00	1,000.00
					ድምር		**7,000.00**	**7,000.00**
1	ኤፊሬም አማረ	13/7/09	JV 885732	6271	በአሶሳ ከተማ ከመጋቢት 05-08/2009 ለተዘጋጀ ስልጠና	2,000.00	1,500.00	3,500.00
2	ቀለሟ መኮንን	13/7/09	JV 885732	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
3	አንዱ አለም አሰፋ	13/7/09	JV 885732	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
4	ጌዲዮን ሙላቱ	13/7/09	JV 885732	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
5	ተመስገን ለታ	13/7/09	JV 885732	6271	›› ››	2,000.00		2,000.00
6	ሰይድ ሀሰን	13/7/09	JV 885732	6271	›› ››	2,000.00		2,000.00
7	ገመቹ አቦሴ	13/7/09	JV 885732	6271	›› ››		500.00	500.00
					ድምር	**12,000.00**	**3,500.00**	**15,500.00**
1	ኤፊሬም አማረ	7/6/09	JV 885654	6271	በላሊበላ ከተማ ከጥር 26-28/2009 ለተዘጋጀ ስልጠና	2,000.00	1,000.00	3,000.00
2	ጥላሁን ገ/ሥላሴ	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››	2,000.00	1,000.00	3,000.00
3	አበራ አንጀሎ	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››	2,000.00	500.00	2,500.00
4	ጌትዬ ተፈራ	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››	2,000.00		2,000.00
5	ጌዲዮን ሙላቱ	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››	2,000.00		2,000.00
6	ሀብታሙ ተስፋዬ	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››	2,000.00		2,000.00
7	ሀይሌ ንጋት	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››		1,000.00	1,000.00
8	ተገኝ ቀናው	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››	2,000.00		2,000.00
					ድምር	**14,000.00**	**3,500.00**	**17,500.00**
					ጠቅላላ ድምር	**54,000.00**	**21,000.00**	**75,000.00**

አባሪ 4 <u>አላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል</u>

ተ ራ ቁ.	ገንዘቡን የወሰደው	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የሂሳብ መደብ	የወጪው ምክንያት	ተከፍሎ የተገኘ ውሎ አበል	የምሳ አበል 25% ተመላሽ የሚሆን
1	ኤፊሬም አማረ	24/4/2009	JV 885581	6271	በአክሱም ከተማ ከታህሳስ 11-13/2009ለተዘጋጀ ስልጠና	660.00	165.00
2	ጥላሁን ገ/ስላሴ	24/4/2009	JV 885581	6271	›› ››	660.00	165.00
3	አበራ አንጅሎ	24/4/2009	JV 885581	6271	›› ››	660.00	165.00
4	ጌትዬ ተፈራ	24/4/2009	JV 885581	6271	›› ››	519.00	129.75
5	መስፈን ጌቴ	24/4/2009	JV 885581	6271	›› ››	378.00	94.50
					ድምር	**2877.00**	**719.25**

6	ለ20 ሰልጣኞች የተከፈለ ውሎ አበል	24/4/2009	JV 885581	6271	›› ››	13,866.00	3,466.50
					ጠቅላላ የተከፈለ	16,743.00	4,185.75
1	ኤፊሬም አማረ	13/7/09	JV 885732	6271	በአሶሳ ከተማ ከመጋቢት 05-08/2009 ለተዘጋጀ ስልጠና	708.00	177.00
2	ቀለሚ መኮንን	13/7/09	JV 885732	6271	›› ››	708.00	177.00
3	አንዱ አለም አሰፋ	13/7/09	JV 885732	6271	›› ››	576.00	144.00
4	ጌዲዮን ሙላቱ	13/7/09	JV 885732	6271	›› ››	576.00	144.00
5	ተመስገን ለታ	13/7/09	JV 885732	6271	›› ››	576.00	144.00
					ድምር	3,144.00	786.00
6	ለ53 ሰልጣኞች የተከፈለ ውሎ አበል	13/7/09	JV 885732	6271	›› ››	35,808.00	8,952.00
					ጠቅላላ የተከፈለ	38,952.00	9,738.00
1	ኤፊሬም አማረ	7/6/09	JV 885654	6271	በላሊበላ ከተማ ከጥር 26-28/2009 ለተዘጋጀ ስልጠና	654.00	163.50
2	ጥላሁን ገ/ሥላሴ	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››	654.00	163.50
3	አበራ አንጀሎ	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››	654.00	163.50
4	ጌትዬ ተፈራ	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››	528.00	132.00
5	ጌዲዬን ሙላቱ	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››	402.00	100.50
					ድምር	2,892.00	723.00
6	ለ63 ሰልጣኞች የተከፈለ ውሎ አበል	7/6/09	JV 885654	6271	›› ››	30,996.00	7,749.00
					ጠቅላላ የተከፈለ	33,888.00	8,472..00
1	ለ56 ሰልጣኞች የተከፈለ ውሎ አበል	13/07/09	JV 885736	6271	በደብረብርሀን ከተማ ከየካቲት 27-መጋቢት01/2009 ለተዘጋጀ ስልጠና	48,335.00	12,083.75
					ጠቅላላ የተከፈለ	137,918.00	34,479.50

አባሪ 5 ተሰብሳቢ ሂሳብ

የሂሣብ መደብ	የሂሣብ መግለጫ	ሰኔ 30/2009 የተመለከተ	የተወራረደ	አሁን የሚገኝበት ሁኔታ		ዝርዝር ሁኔታ
				ያልተወራረደ	ጊዜው ያልደረሰ	
4201	ልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያ	251,479.61	232,357.61	19,122.00		ከ1 ዓመት ከ6 ወራት በላይ የቆየ
4251	ቅድሚያ ክፍያ ለኮንትርክተር	3,114,567.88			3,114,567.88	ከግንቦት/2010 ዓ.ም ጀምሮ
4252	ለአማካሪዎች ቅድሚያ ክፍያ	148,980.00			148,980.00	
4253	ለእቃ አቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ	172,051.50			172,051.50	ከታህሳስ/2010ዓ.ም፡ጀምሮ
4254	ከመንግስት መ/ቤት ውጭ ሌሎች ቅድሚያ ክፍያዎች	345,000.00			345,000.00	ከታህሳስ/2010ዓ.ም፡ጀምሮ
	ድምር	4,032,078.99	232,357.61	19,122.00	3,780,599.38	

አባሪ 6 ከ10% በላይ ሥራ ላይ ያልዋለ መደበኛ በጀት

የሂሳብ መደብ	ወጪ	የተስተካከለ በጀት	ስራ ላይ ያልዋለ	በ %
6213	1,515,673.11	2,661,216.20	1,145,543.09	43.05
6214	8,473.00	13,000.00	4,527.00	34.82
6215	55,652.34	80,000.00	24,347.66	30.43
6217	477,910.12	967,945.00	490,034.88	50.63
6218	511,889.72	670,716.55	158,826.83	23.68
6219	176,121.74	205,517.85	29,396.11	14.30
6223	30,728.07	40,000.00	9,271.93	23.18
6243	120,941.91	655,000.00	534,058.09	81.54
6244	1,166,042.16	4,162,300.00	2,996,257.84	71.99
6231	1,404,432.54	2,001,311.52	596,878.98	29.82
6232	785,954.99	1,001,900.00	215,945.01	21.55
6251	440,640.95	2,064,900.00	1,624,259.05	78.66
6253	901,083.00	1,452,244.80	551,161.80	37.95
6255	65,646.00	131,000.00	65,354.00	49.89
6256	122,606.99	307,510.00	184,903.01	60.13
6257	270,075.28	380,000.00	109,924.72	28.93
6258	577,115.81	2,038,750.00	1,461,634.19	71.69
6259	187,358.39	350,000.00	162,641.61	46.47
6271	3,329,201.10	4,371,533.45	1,042,332.35	23.84
ድምር	**12,147,547.22**	**23,554,845.37**	**11,407,298.15**	**42.66**
6313	1,620,834.07	2,534,606.70	913,772.63	36.05
6314	956,043.93	1,754,940.00	798,896.07	45.52
ድምር	**2,576,878.00**	**4,289,546.70**	**1,712,668.70**	**39.93**
ጠቅላላ ድምር	**14,838,130.97**	**27,999,942.07**	**13,119,966.85**	**47.01**

ካፒታል በጀት

የሂሳብ መደብ	ወጪ	የተስተካከለ በጀት	ለግንባታ ቅድሚያ የተከፈለ	ስራ ላይ ያልዋለ በጀት	በ%
6212	0	30,000.00		30,000.00	100.00
6213	1,104.00	40,000.00		38,896.00	97.24
6217	36,460.88	200,000.00		163,539.12	81.77
6218	0	30,000.00		30,000.00	100.00
6244	17,000,000.00	25,000,000.00	3,263,547.88	4,736,452.12	18.95
6231	246,454.44	300,000.00		53,545.56	17.85
6232	342,652.00	415,000.00		72,348.00	17.43
6251	0	500,000.00		500,000.00	100.00
6258	1,550.00	20,000.00		18,450.00	92.25
ድምር	**17,628,221.32**	**26,535,000.00**	**3,263,547.88**	**5,643,230.80**	**21.27**